# በሁሉም ስርኣት ጠንካራ አመራር እንዲኖር ማድረግ

## አጭር መግለጫ

ጥሩ ውጤት ለማምጣት በእያንዳንዱ አስተዳደርና ደረጃ ውስጥ ጠንካራ የመሪነት ችሎታ ያላቸው መሪዎች እንዲኖሩ ማድረግ።ከእያንዳንዱ ትምህርትቤት እስከ ዋናው ጽህፈትቤትና እንዲሁም የትምህርትቤት ቦርድ ሁሉ ጠንካራ መሪዎች እንዲኖሩ ማድረግ።

በእያንዳንዱ ክፍል ጥሩ መሪዎች እንዳሉ እምነታችን ነው ሆኖም ግን እነዚህ መሪዎች ሃላፊነታቸው በደንብ እንዲወጡ የሚያስፈልገውን እርዳታና ድጋፍ ከኛ እንዳይለያቸው ያስፈልጋል።አሰራራችንም ላይ አስፈላጊውን የአሰራር ለውጥ በማድረግ ጥሩ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሰራተኞች ለመቅጠር መቻል አለብን። በሚቀጥለው አመት የዚሁ አይነት አሰራር ለመገንባት ዲስትሪክቱ ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ በመስጠት ይሰራል።

## ዋና አስፈላጊ ነገሮች

በዚህ አመት የበለጠ ትኩረት የሚሰጣቸው አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች አሉን

**አዲስ ሰራተኛ የመቅጠር አሰራር ላይ ማሻሻል ማድረግ** – የስያትል ህዝባዊ ትምህርትቤቶች አዲስ ሰራተኛ መቀጠር ላይ ያለው አሰራር ከሌሎች ጎረቤት ክልሎች ለየት ያለ አመቺ ያለሆነ አስራር ነው ያለው።በዚሁ ምክንያት ጥራት ያላቸውና ጎበዞች የሆኑ አስተማሪዎች ወደኛ መጥተው ስራ ከማመልከት ይልቅ ወደ ሌላ ክልል ሄደው ለማመልከት ይመርጣሉ።አመልካቾች ወደኛ መጥተው እንዲያመለክቱ የአቀጣጠር አስራራችንን ማሻሻል አድርገናል(ከአስተማሪዎች፤ ርእሰመምህሮችና ሌሎች ሰራተኞች በተገኘው ሃሳብ መሰረት) አዲሱ አሰራር ስራ ላይ እንዲውል አድርገናል።

**የሚጠበቅብን ነገር ማወቅና አስፈላጊውን ድጋፍ ማቅረብ** – አስተማሪዎችና ሁሉም ሰራተኞች ከነሱ የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዲያመጡ ዘንድ ትምህርትቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ ማቅረብ መቻል አለባቸው።ሰራተኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ከተደረገላቸውና ችሎታቸውን ለማሳደግ ይረዳቸዋል።በመጪው ስድስት ወር ውስጥ ከአስተማሪዎች፤ ርእሰ መምህራና ጋር በመተባበር የሚሰጠውን የልዩ ባለሙያዎች እድገት ስልጠና ላይ ግምገማ እናካሂዳለን።በተለይ (በሂሳብና ሳይንስ ) የትምህርት አይነቶች ላይ ልዩ ትኩረት እንዲሰጥበት እናደርጋለን።

**በየአመቱ የሚደረግ ግምገማ አሰራር እንዲኖር ማድረግ** – አብዛኞች የኛ ሰራተኞች ላይ በየአመቱ ችሎታቸው የሚለካበት ግምገማ ይካሄዳል። በዚሁ በሚካሄደው ግምገማ እያንዳንዱ ሰራተኛ ብቃታቸውና ችሎታቸው የሚያሻሽሉበትና ለቀጣይ ፕላን የሚያደርጉበት እንደሚሆን እምነታችን ነው።በመጪው ስድስት ወር ውስጥ ከአስተማሪዎች፤ ርእሰ መምህራና ጋር በመተባበር የሚሰጠውን የልዩ ባለሙያዎች እድገት ስልጠና ላይ ግምገማ እናካሂዳለን።

## ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ጥያቄዎች

- በይበልጥ ለማወቅ የምትፈልጉት ነገር ምንድነው?
- ግልጽ ያልሆነላችሁ ነገር ካለ?
- የጎደለ ነገር ካለ?
- ስለ አሰራራችን ያሉት መረጃዎች ሁሉ በምን መንገድ እንዲደርሳችሁ ትፈልጋላችሁ?